# የብልፅግና ፓርቲ አመራሮችና አባላት ሊያውቋቸውና ሊያከብሯቸው የሚገቡ ምርጫን የሚመለከቱ የአገሪቱ መሠረታዊ ሕጎች

**ጥር 2018 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ**

# የብልፅግና ፓርቲ አመራሮችና አባላት ሊያውቋቸውና ሊያከብሯቸው የሚገቡ ምርጫን የሚመለከቱ የአገሪቱ መሠረታዊ ሕጎች

## 1. የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት(1987)

### 1.1. የሕገ መንግሥት የበላይነት(አንቀጽ 9)

1) ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው። ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም።
2) ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው፣ ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።
3) በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

### 1.2. የመምረጥና የመመረጥ መብት(አንቀጽ 38)

1) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት፤

   ሀ/ በቀጥታ እና በነጻነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣

   ለ/ ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሰረት የመምረጥ ፣

   ሐ/ በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ። ምርጫው ሁሉ አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነጻነት የሚገልጽበት ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት።

2) በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሠሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በፍላጐቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት።
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነጻና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈጸማሉ።

### 1.3. **የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት(አንቀጽ 54)**

1) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፤ ሁሉ አቀፍ፣ ነጻ ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ።
2) የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ። የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸው አናሳ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በምርጫ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ይሆናሉ።

### 1.4. **የፖለቲካ ሥልጣን(አንቀጽ 56)**

በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች የፌዴራሉን መንግሥት የሕግ አስፈጻሚ አካል ያደራጃል/ያደራጃሉ፤ ይመራል/ይመራሉ።

### 1.5. **የምክር ቤቱ ስብሰባና የሥራ ዘመን(አንቀጽ 58)**

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጠው ለአምስት ዓመታት ነው፤ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል።

### 1.6. **በሁለቱም ምክር ቤቶች አባል መሆን የማይቻል ስለመሆኑ(አንቀጽ 68)**

ማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ሊሆን አይችልም።

### 1.7. **የምርጫ ቦርድ(አንቀጽ 102)**

- በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል።

## 2. <u>በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1162/2011) እና ማሻሻያው (አዋጅ ቁጥር 1394/2017)</u>

### 1. በምርጫ ስለሚወዳደሩ የመንግሥት ሰራተኞች(አንቀጽ 33)

- ዳኞች፣ ዓቃቤ ሕጎች፣ ወታደሮች፣ ፖሊስ እና ሌሎች የጸጥታ ሃይሎች፣ የደህንነት ሰራተኞች፣ እና የቦርዱ ሰራተኞች በግል ወይም የፖለቲካ ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ ሆነው ከቀረቡ የያዙትን የመንግሥት ሥራ መልቀቅ አለባቸው(**አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ** 2)፣

- ዳኞች፣ ዐቃቤ ሕጎች፣ ወታደሮች፣ ፖሊስ እና ሌሎች የጸጥታ ሃይሎች፣ የደህንነት ሰራተኞች እና የቦርዱ ሰራተኞች በምርጫ ውድድር ጊዜ ማንኛውንም ተወዳዳሪ ለማስመረጥ በመደገፍ፣ በመናገር፣ በመፃፍና በመሳሰሉት ተሳታፊ መሆን የለባቸውም(**አንቀጽ** 33 **ንዑስ አንቀጽ** 2)።

2. **ከዕጩነትና ጋር የተያያዙ መብቶች**
   - ***የመንግሥት ሠራተኞች ዕጩነት፦*** *ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ዕጩ ሆኖ ሲቀርብ ከዕጩነት ምዝገባው ቀን ጀምሮ ምርጫው ተካሂዶ ውጤቱ እስከሚገለጽበት ጊዜ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከደመወዝ ጋር ፈቃድ የማግኘት መብት አለው።* (**አንቀጽ** 29 **ንዑስ አንቀጽ** 2)
   - ***የዕጩዎች ልዩ መብት፦*** *ማንኛውም ዕጩ የምርጫው ውጤት ይፋ እስከሚደረግበት ጊዜ ድረስ ከባድ ወንጀል ፈጽሞ እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር በወንጀል አይያዝም፤ ክስም አይመሰረትበትም።* (**አንቀጽ** 30 **ንዑስ አንቀጽ** 1)

3. **በአንድ ምርጫ ክልል ብቻ ስለመወዳደር(አንቀጽ** 41)
   1) *አንድ ሰው በእጩ ተወዳዳሪነት መቅረብ የሚችለው በአንድ የምርጫ ክልል ብቻ፣ ለአንድ የሕዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤት ወንበር ብቻ ይሆናል።*
   2) *አንድ እጩ ተወዳዳሪ በእጩዎች ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ከአንዱ የምርጫ ክልል ወደ ሌላው የምርጫ ክልል ተዛውሮ በህጉ መሠረት እንደ አዲስ ተመዝግቦ ለመወዳደር ይችላል።*

4. **የምርጫ ቅስቀሳ መብትና ገደብ**
   - ***የቅስቀሳ ጊዜ ገደብ፦*** *ማንኛውም የምርጫ ቅስቀሳ ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ* 4 *ቀናት በፊት መጠናቀቅ አለበት።* (**አንቀጽ** 42 **ንዑስ አንቀጽ** 4)
   - ***የምርጫ ቅስቀሳ መብት፦*** *የፖለቲካ ፓርቲዎችና ዕጩዎች የምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሲያዘጋጁ የሚመለከተውን የመንግሥት አካል ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልጋቸው፤ ለሚመለከተው አካል በጽሑፍ በማሳወቅ ብቻ ማከናወን ይችላሉ።* (**አንቀጽ** 43 **ንዑስ አንቀጽ** 1)

5. **የመንግሥት አካላት ግዴታ(አንቀጽ** 45)

*የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴዎችን ለማሳካት በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት አካላት ኃላፊዎች የሚያስተዳድሯቸውን የሬድዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን፣ ጋዜጦችና*

እንዲሁም የስብሰባ አዳራሾች፣ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ያለአድልዎ እንዲገለገሉባቸው ለማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ አለባቸው።

6. **የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም(አንቀጽ 48)**
    1) በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉትን መገናኛ ብዙኃን ማለትም ሬድዮ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጦችን ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለ አድልዎ የመጠቀም መብት አላቸው።
    2) እጩዎች በመንግሥት የመገናኛ ብዙኃን ነፃ የአየር ጊዜ አግኝተው የመጠቀም መብት አላቸው።
    3) መንግሥት የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀምን በተመለከተ ቦርዱ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶችን ባሳተፈ አካሄድ በሚያወጣው የድልድል መመሪያ መሠረት ይከናወናል።
    4) የመንግሥትም ሆነ የግል የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም፥ የጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ እና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን የሚመለከቱ የሥነ ምግባር እና የአፈጻጸም መርሆችን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል ።

7. **የምርጫ ሥነ-ምግባር**
    - **የሌሎችን እንቅስቃሴ ማደናቀፍ፡-** የሌሎች ፓርቲዎችን ፖስተሮች ማበላሸት፣ መቀደድ ወይም ሰላማዊ ስብሰባዎቻቸውንና ሰልፎቻቸውን በአመራሩ ወይም በአባላቱ አማካኝነት ማወክና ማደናቀፍ የተከለከለ ነው። (**አንቀጽ** 129 **ንዑስ አንቀጽ** 1 **ሐ እና መ**)
    - **የጥላቻ ንግግርና ቅስቀሳ፡-** በማንኛውም መገናኛ ብዙኃን አመጽ የሚቀሰቅስ፣ ግጭት የሚቀሰቅስ ወይም ጥላቻን የሚያበረታታ ንግግር ማድረግ፣ ጽሑፍ ማሰራጨት ወይም ምልክት ማሳየት የተከለከለ ነው። (**አንቀጽ** 132 **ንዑስ አንቀጽ** 3)
    - **ምልክቶችንና ንብረትን መጠበቅ፡-** የሌሎች ፓርቲዎችን አርማ ማመሳሰል ወይም የምርጫ ቁሳቁሶችን መስረቅና ማበላሸት የተከለከለ ነው። (**አንቀጽ** 133)
    - **ሁከትና አመጽ፡-** ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ዕጩ በማንኛውም የሁከት ወይም የአመጽ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ወይም እንዲደረግ መፍቀድ የለበትም። (**አንቀጽ** 134 **ንዑስ አንቀጽ** 3 **ሀ**)

8. **የመንግሥት ሥልጣንና ሀብትን በአግባቡ መጠቀም**

- ***ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም፦*** *ያለውን የሥልጣን ኃላፊነትና ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ ለፖለቲካ ፍላጎት መደለያነት መጠቀም የተከለከለ ነው ።* **(አንቀጽ 135 ንዑስ አንቀጽ 1 ሀ)**
- ***የመንግሥት ሀብት፦*** *የመንግሥትን መሠረተ ልማትና ሀብት (ተሽከርካሪዎችንና ሌሎች ንብረቶችን) ለምርጫ ቅስቀሳና ለፓርቲ ተግባራት መጠቀም አይፈቀድም ።* **(አንቀጽ 135 ንዑስ አንቀጽ 1 ለ)**
- ***የሠራተኛ መዋጮ፦*** *ከመንግሥት ወይም ከልማት ድርጅት ሠራተኛ ደመወዝ ላይ የአባልነት መዋጮን በቀጥታ መቀነስ ወይም መሰብሰብ አይቻልም ።* **(አንቀጽ 142)**

9. **የፓርቲው አስተዳደራዊ ግዴታዎች**

- ***ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች፦*** *ፓርቲው ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሲያቋቅም አድራሻውንና የኃላፊዎቹን ስም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማሳወቅ ይኖርበታል።* **(አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 5)**
- ***መረጃ የመስጠት ግዴታ፦*** *ፓርቲው በአዋጁ የተዘረዘሩ መረጃዎችን እንዲያቀርብ በቦርዱ ሲጠየቅ የጽሑፍ መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት።* **(አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1)**
- ***የመታገድ ምክንያቶች፦*** *አንድ ፓርቲ የኦዲት ሪፖርት ካላቀረበ፣ አባላትን በኃይል ካስገደደ ወይም የሌሎች ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ ካደናቀፈ ቦርዱ እስከ 5 ዓመት ሊያግደው ይችላል።* **(አንቀጽ 98 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2)**
- ***የሂሳብ ሪፖርት፦*** *ማንኛውም ፓርቲ በየዓመቱ በራሱ ኦዲተር የሂሳብ ምርመራ በማካሄድ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስተኛው ወር ለቦርዱ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።* **(አንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ 1)**

10. **ስለ ጋዜጠኞች አንቀጽ 126)**

1) *የምርጫ ሂደትን መዘገብ የሚፈልግ ጋዜጠኛ ስራውን የሚገልጽ መታወቂያና ከሚሰራበት የመገናኛ ብዙኃን ተቋም የተሰጠ ማረጋገጫ በመያዝ የምርጫውን ሂደት መከታተል ይችላል። ከምርጫ ጣቢያ ፪ መቶ ሜትር ርቀት ዙሪያ ውስጥ ገብቶ ለመዘገብ የፈለገ ጋዜጠኛ ከምርጫው ቀን አስቀድሞ ከቦርዱ ፈቃድ ማግኘት አለበት።*

2) ማንኛውም ጋዜጠኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) የተጠቀሰውን ሥራውን ሲያከናውን በመራጮች ውሳኔ ላይ እና ምርጫ አስፈጻሚዎች ተግባራት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድር ድርጊት መቆጠብ አለበት።

3) ማንኛውም ጋዜጠኛ ቦርዱ ከዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ መንገድ የሚያወጣውን የምርጫ አዘጋገብ የሥነ ምግባር ደንብ ማክበር አለበት።

11.አባላትን የማስተማርና የማውገዝ ኃላፊነት

- **የሥነ-ምግባር ትምህርት፦** ፓርቲው አባላቱና ደጋፊዎቹ የአዋጁን ድንጋጌዎች እንዲያከብሩ የማስተማርና ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለበት ። (አንቀጽ 128 ንዑስ አንቀጽ 2)
- **ሕገ-ወጥ ድርጊትን ማውገዝ፦** ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በአባላቱ ወይም በደጋፊዎቹ የተፈጸመን የአመጽ ድርጊት ወይም ለአመጽ የሚጋብዝ ተግባር በይፋ የማውገዝ ግዴታ አለበት። (**አንቀጽ** 128 **ንዑስ አንቀጽ** 3)

12. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት

- **ይግባኝ፦** ቦርዱ በሚያስተላልፈው የእገዳ ወይም የምዝገባ ስረዛ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ፓርቲ በ30 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። (**አንቀጽ** 100 **ንዑስ አንቀጽ** 1)
- **የወኪሎች መብት፦** ማንኛውም የፓርቲ ወኪል በምዝገባ ሂደት ላይ ተቃውሞ ካለው ወዲያውኑ ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ማቅረብ ይችላል።(**አንቀጽ** 148 **ንዑስ አንቀጽ** 1)
- **የድምፅ ቆጠራ ቅሬታ፦** በድምፅ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ ላይ ቅሬታ ያለው ወኪል ቅሬታውን ወዲያውኑ ለጣቢያው ኃላፊ ማቅረብ ይኖርበታል፤ ኃላፊውም በ12 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል። (**አንቀጽ** 150 **ንዑስ አንቀጽ** 1 **እና** 2)

13. የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል ዕጩ ወኪሎች(**አንቀጽ** 118)

1) ማንኛውም ለምርጫ ዕጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ የምርጫውን ሂደት የሚከታተሉ:-

ሀ) ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት ሁለት እየተቀያየሩ የሚሰሩ ተቀማጭ ወኪሎች፤

ለ) በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ስር በሚገኝ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ እየተቀያየሩ በጣቢያው የሚሰሩ ሁለት ተቀማጭ ወኪሎችን፤ መሰየም ይችላል።

2) ማንኛውም የግል ዕጩ:-

ሀ) በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽ/ቤት ሁለት እየተቀያየሩ የሚሰሩ ተቀማጭ ወኪሎች፤

ለ) በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ስር በሚገኝ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ በፈረቃ በጣቢያው የሚቀመጡ ሁለት ወኪሎችን፤ መሰየም ይችላል።

3) እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ በአንድ የምርጫ ክልል ከሰባት የማይበልጡ ተዘዋዋሪ ወኪሎችን መመደብ ይችላል።

## 14. የወኪሎችን ስም ዝርዝር ስለማሳወቅ(አንቀጽ 119)

1) ማንኛውም ዕጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ የተቀማጭና የተዘዋዋሪ ወኪሎችን ስም ዝርዝር ተጠባባቂ ወኪሎችን ጨምሮ ከድምፅ መስጫው ዕለት ሰባት ቀን አስቀድሞ ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት። የምርጫ ክልሉ ኃላፊም የታዛቢዎቹ ስም ዝርዝር የያዘ ደብዳቤ ዝርዝሩ በደረሰው በሁለት ቀናት ውስጥ ለፖለቲካ ፓርቲው መስጠት አለበት።

2) የምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በየምርጫ ጣቢያው የተመደቡ ተቀማጭና ተዘዋዋሪ ወኪሎችን ለየምርጫ ጣቢያው በወቅቱ ያሳውቃል።

## 15.የምርጫ ሥነ ምግባር ድንጋጌዎች(መርህ) አንቀጽ 127))

1) በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ሥርዓት የሚመረጥ መንግሥት ህጋዊነት በሚከተሉት መርሆዎች ላይ ይመሠረታል:-

ሀ) መራጮች በምርጫ ዘመቻው አማካኝነት ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲዎችና ስለ እጩዎች ማንነት የተሟላ መረጃ ሲሰጣቸውና የራሳቸውን በእውቀት ላይ በተመሰረተ እና ከግል ፍላጎት የሚመነጭ ውሳኔ ሲያደርጉ፤ እና

ለ) መራጮች በነፃነት፣ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት፣ ያለፍርሃት፣ ያለተፅእኖ፣ ያለጫና፣ እንዲሁም ከጉቦ እና ከተለያዩ መደለያዎች ነፃ በሆነ መልኩ ድምፅ መስጠት፤ ሲችሉ ነው።

2) ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በቅን ልቦና እየተመሩ:-

ሀ) የምርጫ ሥነ ምግባር መርሆዎች እንዲከበሩ፤

ለ) ምርጫ የመላው ህዝብ ነፃ እና ተቀባይነት ያለው ውሳኔ መግለጫ ሆኖ እንዲታወቅ፤

ሐ) የመራጩ ህዝብ ውሳኔ በሁሉም ዘንድ የተከበረ እንዲሆን፣ መስራት አለባቸው።

3) ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዙ ማናቸውም ጉዳዮች ዙሪያ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል እጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ አዋጅ ጋር በተጣጣመ አኳኋን መንቀሳቀስ አለባቸው።

## 16. ለአዋጁ የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች መገዛት(አንቀጽ 128)

1) ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ተወዳዳሪ:-

ሀ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት መንቀሳቀስ አለበት፤

ለ) መሪዎቹ፣ ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹ እና አባላቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እንዳይጥሱ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት፤

ሐ) የፓርቲው ኃላፊዎች እጩዎችና አባላት የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚጥስ ተግባር እንዳይፈጽሙ፤ ደጋፊዎቹም የተከለከሉ ድርጊቶች ከመፈጸም እንዲቆጠቡ ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፣

መ) ዓላማ እና ፕሮግራማቸውን ወደ ሕዝብ በሚያደርሱበት ጊዜ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ያለ አድልዎ ተፈጻሚ ማድረግ አለባቸው።

2) የፓርቲው አባላት ወይም ደጋፊዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲያከብሩ ቦርዱ በሚያወጣው ዕቅድ መሠረት ማስተማርና ሌሎች ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች መውሰድ አለበት።

3) ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሥነ-ምግባር የሚያስተምሩበትና አቋማቸውን የሚገልጹበትን መንገድ እንዲሁም የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማቸውን አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያዎችን ያወጣል።

## 17.የምርጫ ዘመቻ አካሄድ(አንቀጽ 129)

1) ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ) የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ የማካሄድ የፖለቲካ ሀሳቦችንና መርሆዎቻቸውን ያለ ስጋት የማሰራጨት መብቶቻቸውን ማክበር፤

ለ) እንቅስቃሴው የሌላውን የፖለቲካ ፓርቲ፣ የመራጩን ሕዝብ እና የሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች መብቶችን ያከበረ መሆን፤

ሐ) የመገናኛ ብዙኃን ነፃነትን ማክበር፤

መ) ተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጩ ሕዝብ ያላቸውን የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ማክበር፤

ሠ) በፖለቲካ እንቅስቃሴ ለመሳተፍ የሚሹ የመምረጥና የመመረጥ መብት ያላቸው ዜጎች ሁሉ በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ፤ አለበት።

2) ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ) የግል ወይም የመንግሥት ጋዜጠኞች በሙያዊ ስራቸው ላይ እንዳይሰማሩ ማዋከብ፣ እንቅፋት መፍጠር፤ በማንኛውም አይነት ድርጊት የሌሎች ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጎል፣ እንዲቋረጥ፣ እንዲበላሽ፣ እንዲዳከም ማድረግና መተባበር፤

ለ) የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ማስታወቂያ፣ በራሪ ጽሑፍ ወይም ፖስተር እንዳይሰራጭ ማወክ፤

ሐ) የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች ፖስተሮችን ማበላሸት፣ ማጥፋት ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ እንዳይታዩ ወይም እንዳይነበቡ ማድረግ፤

መ) ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባ፥ የእግር ጉዞ፥ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያደርግ በአመራሩ፣ በአባላቱ፣ ወይም በደጋፊዎቹ አማካኝነት ማገድ፣ ማወክ፣ ቅስቀሳ ማድረግ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ማደናቀፍ፤

ሠ) ማንኛውም ሰው በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ ድጋፍ ሰልፍ እንዳይሳተፍ መከልከል፤

ረ) ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከሉ ማናቸውንም ተግባራት እንዲፈፅሙ መቀስቀስና ማነሳሳት፤ የለበትም።

18. ከአንቀጽ 130 እስከ 137 መነበብ አለባቸው።

19. **የፖለቲካ ፓርቲዎችና እጩ ተወዳዳሪዎች ኃላፊነት(አንቀጽ 138)**

1) ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ ይህ የምርጫ አዋጅ በመራጩ ህዝብ ዘንድ እንዲታወቅ የበኩሉን ጥረት ማድረግ አለበት፤ በተለይም አዋጁን ለእጩዎቹ ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ በማስተማር በሁሉም ዘንድ መታወቁንና መከበሩን ማረጋገጥ አለበት።

2) እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በምርጫው ሂደት የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ለመራጮች ለማስተማር የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍና ማስተዋወቅ አለበት።

3) ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ:-

ሀ/ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ማክበር፤

ለ/ እጩዎቹ ባለስልጣኖቹ፣ ወኪሎቹ፣ አባሎቹና ደጋፊዎቹ ይህን አዋጅ አክብረው እንዲንቀሳቀሱ መምራት እና ማክበራቸውንም የሚያረጋግጡ ተገቢ እርምጃዎች መውሰድ፤ አለበት።

4) ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ ፤ሁሉም ሰው:-

ሀ) የፖለቲካ እምነቱን እና አስተያየቱን በነፃ የመግለፅ፤

ለ) በሌሎች የፖለቲካ እምነት እና አስተያየት ላይ የመከራከር እና የመተቸት፤

ሐ) የራሱን የምርጫ ቅስቀሳ ቁሳቁሶች የማተምና የማሰራጨት፤

መ) ፖስተሮችን፣ ባነሮችንና ቢልቦርዶችን የመስቀል፤

ሠ) ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ማንኛውም ዓይነት ገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሰው ኃይል የምርጫ ድጋፍ የማሰባሰብ፤

ረ) አባላትን የመመልመል፤

ሰ) ህዝባዊ ስብሰባዎችን የማካሄድ፤

ሸ) በህዝባዊ ስብሰባዎች የመገኘት፤ መብቶች እንዳሉት በይፋ የመግለፅ፤ ግዴታ አለበት።

5) የፖለቲካ ፓርቲዎችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች አዋጁንና በአዋጁም ለመገዛት ያላቸውን ቁርጠኝነት ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለባቸው።

6) የፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩ ተወዳዳሪዎች ነፃና ፍትሀዊ ምርጫን የሚጎዳ ወይም የሚያጣጥል ማንኛውንም ተግባር በይፋ ማውገዝ አለባቸው።

## 20. የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ማደናቀፍ (አንቀጽ 145)

ማንኛውም የፖለቲካፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ:-

1) ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል እንዳይመለምልና ጽህፈት ቤት እንዳይከፍት በማናቸውም መንገድ ያደናቀፈ፣ ወይም የተከፈቱ ጽህፈት ቤቶች በነፃነት እንዳይሠራባቸው በግልፅም ሆነ በስውር ያወከ ወይም ሁከት እንዲፈጠር ያደረገ ወይም በማንኛውም ዓይነት ድርጊት የማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ የምርጫ እንቅስቃሴ ያደናቀፈ፣

2) ፓርቲዎች ያዘጋጁት የድርጅት ልሳን፣ የምርጫ ማስታወቂያ፣ በራሪ ጽሑፍ፥ ወይም ፖስተር እንዳይሰራጭ፣ እንዳይታይ ወይም እንዲበላሽ ያደረገ ወይም እንዳይለጠፍ ያወከ ወይም የተለጠፈውን የቀደደ፣ ያበላሸ፣ ያነሳ፥ ያጠፋ፣

3) የሌላን የፖለቲካ ፓርቲ ምልክት ወይም አርማ የቀዳ ወይም አስመስሎ የተጠቀመ፣

4) የሌላ ፖለቲካ ፓርቲን የምርጫ ቁሳቁስ የሰረቀ ወይም ያበላሸ ወይም ያጠፋ አንደሆነ፤ የሥነ ምግባር ጥሰት እንደፈፀመ ይቆጠራል።

## 21.ከጋዜጠኞች ወይም ከታዛቢዎች ጋር አለመተባበር(አንቀጽ 146)

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ:-

1) የመገናኛ ብዙኃንን ነፃነትን የተጋፋ፣

2) በምርጫ ሂደት ጋዜጠኛን ያዋከበ ወይም ሥራውን ያደናቀፈ፤

3) የተፈቀደላቸውን ታዛቢዎች ያላከበረ ወይም ያልተባበረ እንደሆነ፤ የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል።

## 22.የሥነ ምግባር ድንጋጌዎቹን አለማስተዋወቅና ሕገ ወጥ ድርጊቶችን አለማውገዝ (አንቀጽ 147)

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ:-

1) በአባሉ፣ በአቀረበው እጩ ተወዳዳሪ ወይም በመሪው የተፈፀመን የአመፅ ድርጊት ወይም ለአመፅ የሚጋብዝ ተግባር በይፋ ማውገዝ ሲገባው ያላወገዘ።

2) ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹ፣ አባላቱና ደጋፊው መቼም፣ ማንንም ማስፈራራት እንደሌለባቸው በግልጽ የሚከለክል መመሪያ ያላወጣ እንደሆነ፤

3) የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ተቆጥሮ ቦርዱ የሚወስነውን ቅጣት የሚፈጸምበት ሲሆን የፈጸመው ጥፋት በሌሎች ሕጎችም የሚያስቀጡ እንደሆነ ቦርዱ ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል ሊመራው ይችላል።

## 3. <u>በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለምርጫ ቅስቀሳ አገልግሎት የመንግሥት አዳራሾችን አጠቃቀም ለመደንገግ የወጣ መመሪያ</u>

**ክፍል አንድ፡ የአዳራሽ ጥያቄና አጠቃቀም መርሆዎች**

- **ፍትሐዊ ተጠቃሚነት፦** *ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ የመንግሥት አዳራሾችን ለምርጫ ቅስቀሳ አገልግሎት በእኩልነትና በፍትሐዊነት የመጠቀም መብት አለው።* (**አንቀጽ** 4)
- **ቅድሚያ የማሳወቅ ግዴታ፦** *አንድ ፓርቲ አዳራሽ ለመጠቀም ሲፈልግ ስብሰባው ከመካሄዱ* **ቢያንስ 72 ሰዓት (3 ቀናት) በፊት** *ለአዳራሹ ባለቤት ወይም ለሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።* (**አንቀጽ** 6 **ንዑስ አንቀጽ** 1)
- **የማሳወቂያ ደብዳቤ ይዘት፦** *ጥያቄው የስብሰባውን ዓላማ፣ የሚካሄድበትን ቀን፣ የሚጀምርበትንና የሚያልቅበትን ሰዓት እንዲሁም የሚጠበቀውን የታዳሚ ብዛት መያዝ አለበት።* (**አንቀጽ** 6 **ንዑስ አንቀጽ** 2)
- **የተቋሙ ምላሽ፦** *አዳራሹን የሚያስተዳድረው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጥያቄው በደረሰው በ24 ሰዓት ውስጥ ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት።* (**አንቀጽ** 6 **ንዑስ አንቀጽ** 5)
- **የክፍያ ሁኔታ፦** *ፓርቲው ለአዳራሹ የሚከፈለው ክፍያ ካለ፣ ተቋሙ ለሌሎች መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከሚያስከፍለው ተመን መብለጥ የለበትም።* (**አንቀጽ** 7 **ንዑስ አንቀጽ** 1)

**ክፍል ሁለት፡ በአዳራሽ አጠቃቀም ወቅት የተከለከሉ ድርጊቶች (አንቀጽ 10)**

*የፓርቲው አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች በአዳራሹ ውስጥ በሚገኙበት ወቅት የሚከተሉትን ድርጊቶች ከመፈጸም መቆጠብ አለባቸው፡-*

1. **የጦር መሣሪያ ክልከላ፦** *በስብሰባ አዳራሽ ውስጥ የጦር መሣሪያዎችን፣ ሌሎች ጉዳት አድራሽ መሣሪያዎችን ወይም የእነዚህን ምስሎች ይዞ መገኘት ወይም ማሳየት።* (**አንቀጽ** 10 **ንዑስ አንቀጽ** 1)

2. **አግባብ ያልሆነ ተፅዕኖ፦** የፓርቲውን ተቀባይነት ወይም የአባላትን ብዛት አላግባብ በመጠቀም በሌሎች ዕጩዎች ላይ ተፅዕኖ መፍጠር ወይም ማስፈራራት። (**አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ** 2)
3. **የንብረት ጥበቃ፦** የአዳራሹን ንብረት፣ የድምፅ መሣሪያዎችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን በአግባቡ አለመያዝ ወይም ጉዳት ማድረስ። (**አንቀጽ** 10 **ንዑስ አንቀጽ** 3)
4. **ጸያፍ ድርጊቶች፦** ማንኛውንም ዓይነት የሥነ-ምግባር ጉድለት፣ ጸያፍ ንግግር ወይም የሌሎችን ክብር የሚነኩ ተግባራትን መፈጸም። (**አንቀጽ** 10 **ንዑስ አንቀጽ** 4)
5. **የአገልግሎት ለውጥ፦** አዳራሹን ከተፈቀደለት የምርጫ ቅስቀሳ ዓላማ ውጭ ለሌላ ተግባር መጠቀም። (**አንቀጽ** 10 **ንዑስ አንቀጽ** 5)

**ክፍል ሦስት፡ የአስተዳደራዊ እርምጃዎች**

- **የቅሬታ አቀራረብ፦** አንድ ፓርቲ አዳራሽ ተከልክያለሁ ብሎ ካመነ ወይም አድሎ ተፈጽሞብኛል ካለ ለቦርዱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። (**አንቀጽ** 11 **ንዑስ አንቀጽ** 1)
- **የተቋማት ኃላፊነት፦** አዳራሽ ለመፍቀድ ፈቃደኛ ያልሆኑ ወይም አድሎ የፈጸሙ የመንግሥት ተቋማት ኃላፊዎች በሕግ ተጠያቂ ይሆናሉ። (**አንቀጽ** 13)

## 4. <u>በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የወጣው የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 14/2013</u>

1. **የምርጫ ታዛቢዎችና ወኪሎች ስለመመደብ**
   - **የፓርቲ ወኪሎች ምደባ፦** ማንኛውም በምርጫው የሚወዳደር የፖለቲካ ፓርቲ በየምርጫ ጣቢያው ድምፅ አሰጣጥንና ቆጠራን የሚታዘቡ **ሁለት ወኪሎችን** የመመደብ መብት አለው። (**አንቀፅ** 8 **ንዑስ አንቀፅ** 1)
   - **የወኪሎች መታወቂያ፦** የፓርቲ ወኪሎች በቦርዱ የተሰጣቸውን መታወቂያ በግልጽ በሚታይ ቦታ የማሰር ግዴታ አለባቸው። (**አንቀፅ** 8 **ንዑስ አንቀፅ** 4)
2. **በድምፅ አሰጣጥ ሂደት የወኪሎች መብትና ግዴታ**
   - **የድምፅ መስጫ ሳጥን ምርመራ፦** ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ በፊት የፓርቲ ወኪሎች የድምፅ መስጫ ሳጥኑ ባዶ መሆኑን የማረጋገጥና በሳጥኑ ላይ ማህተም ሲደረግ የመታዘብ መብት አላቸው። (**አንቀፅ** 14 **ንዑስ አንቀፅ** 1)

- **ድምፅ አሰጣጥን መታዘብ፦** ወኪሎች በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ በመገኘት ሂደቱን የመታዘብና ግድፈት ካለ ቅሬታ የማቅረብ መብት አላቸው። (**አንቀፅ** 17)
- **ሚስጥራዊነትን ማክበር፦** ማንኛውም ወኪል መራጩ ድምፅ የሚሰጥበትን ሚስጥር የመጠበቅና ጣልቃ አለመግባት ግዴታ አለበት። (**አንቀፅ** 23)

3. **በድምፅ ቆጠራ ሂደት የወኪሎች ተሳትፎ**
   - **በቆጠራው መገኘት፦** የፓርቲ ወኪሎች የድምፅ ቆጠራው ሲከናወን በቅርብ ርቀት የመታዘብ መብት አላቸው። (**አንቀፅ** 37 **ንዑስ አንቀፅ** 1)
   - **ስለማይጸኑ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች፦** የትኞቹ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች አይጸኑም (ውድቅ ይሆናሉ) በሚለው ውሳኔ ላይ ወኪሎች አስተያየት የመስጠት መብት አላቸው። (**አንቀፅ** 42)
   - **የቆጠራ ውጤት ቅጽ መፈረም፦** ቆጠራው ሲጠናቀቅ ወኪሎች በውጤት መግለጫ ቅጽ ላይ የመፈረም ግዴታ አለባቸው። ቅሬታ ካላቸው ግን ቅሬታቸውን በመመዝገብ መፈረም ይችላሉ። (**አንቀፅ** 47 **ንዑስ አንቀፅ** 1 **እና** 2)
   - **የውጤት ኮፒ የማግኘት መብት፦** የጣቢያው የምርጫ ውጤት ከተረጋገጠ በኋላ ለእያንዳንዱ የፓርቲ ወኪል የውጤቱ ትክክለኛ ግልባጭ (ኮፒ) የመስጠት ግዴታ አለበት። (**አንቀፅ** 47 **ንዑስ አንቀፅ** 4)
4. **ቅሬታ አቀራረብና ክልከላዎች**
   - **ቅሬታ የማቅረብ መብት፦** በድምፅ አሰጣጥ ወይም በቆጠራ ሂደት ግድፈት አለ ብሎ የሚያምን ወኪል ቅሬታውን ለጣቢያው ኃላፊ ወዲያውኑ ማቅረብ አለበት። (**አንቀፅ** 51)
   - **ቅሬታን በጽሑፍ ስለማስፈር፦** የቀረበው ቅሬታና የተሰጠው ውሳኔ በቅሬታ መዝገብ ላይ መስፈር እንዳለበት የመከታተል መብት አላቸው። (**አንቀፅ** 52)
   - **የተከለከሉ ድርጊቶች፦** ወኪሎች በምርጫ ጣቢያ ውስጥ ቅስቀሳ ማድረግ፣ ለመራጮች አቅጣጫ ማሳየት ወይም በምርጫ አስፈጻሚዎች ሥራ ውስጥ ጣልቃ መግባት በጥብቅ የተከለከለ ነው። (**አንቀፅ** 57)

5. <u>በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የወጣውን የመገናኛ ብዙሃን እና የጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ የሥነ-ምግባር እና አሰራር መመሪያ ቁጥር 02/2013</u>

1. ስለፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩ ተወዳዳሪዎች ኃላፊነት(**አንቀፅ** 27)

ማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ፣

1. የመገናኛ ብዙሀን ነፃነት ማክበር አለበት፣
2. ጋዜጠኞችን ማዋከብ፣ ሙያዊ ተግባራቸውን ማደናቀፍ ወይም ማወክ የለበትም።
3. የያዘውን የስራ ኃላፊነት ወይም ስልጣን ተጠቅመው ፍትሀዊ ያልሆነ የመገናኛ ብዙሀን ተጠቃሚ ከመሆን መቆጠብ አለበት።
4. ለመገናኛ ብዙሀንም ሆነ ለጋዜጠኛ ምንም አይነት ስጦታ፣ ጉቦ ወይም የተስፋ ቃል መስጠት የለበትም።
5. የሌላ ፓርቲን ወይም እጩን አስመልክቶ የተገለፀ አቋምን እና መረጃዎችን አዛብቶ ማቅረብ የለበትም።
6. መገናኛ ብዙሃን በምርጫው ሂደት ተገቢ ሚናቸውን እንዲጫወቱ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት፤
7. ወኪሎቹ ወይም ደጋፊዎቹ በጋዜጠኞች ላይ ጥቃት፣ ማስፈራራት፣ አደጋ፣ ጫና እና ድብደባ እንዳያደርሱ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት።
8. በምርጫ ዘመቻ ወቅት መቻቻልና ነፃ ክርክር እንዲረጋገጥ ተገቢውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል።

## 6. <u>በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የወጣውን በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚደረግ ውይይት የሚመራበት መመሪያ (ጥር 2014 ዓ.ም የተሻሻለ)</u>

1. **የውይይቱ ዓላማዎችና መርሆዎች**
   - **የትብብርና የመተማመን መርህ፡-** በፓርቲዎች መካከል ያለውን አለመተማመን በማስወገድ የጋራ ራዕይ መገንባትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ላይ በትብብር መሥራት። (**አንቀጽ** 1)
   - **ሐቀኝነትና ቅንነት፡-** የውይይቱ ተሳታፊዎች በውይይት ወቅት ለሚያነሷቸው ጉዳዮች ሐቀኞችና ቅን መሆን ይኖርባቸዋል። (**አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ** 1)
   - **ውይይትን ለሰላም መጠቀም፡-** የፖለቲካ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና ግጭቶችን ለማስወገድ ውይይትን እንደ ዋና መሣሪያ መጠቀም። (**አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ** 3)
2. **የውይይት ተሳታፊዎች መብትና ግዴታዎች**
   - **ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት፡-** ማንኛውም በውይይቱ ላይ የሚሳተፍ የፓርቲ ተወካይ በውይይቱ አጀንዳ ላይ ያለውን ሐሳብ በነፃነት የመግለጽ መብት አለው። (**አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ** 1)

- **የመደመጥ መብት፦** ተሳታፊዎች ሐሳባቸውን በሚገልጹበት ወቅት ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመደመጥ መብት አላቸው። (**አንቀጽ** 10 **ንዑስ አንቀጽ** 2)
- **መረጃ የማግኘት መብት፦** ስለ ውይይቱ ሂደትና ስለሚወሰኑ ውሳኔዎች መረጃ የማግኘት መብት። (**አንቀጽ** 10 **ንዑስ አንቀጽ** 4)
- **የሥነ-ምግባር ግዴታ፦** ተሳታፊዎች በውይይት ወቅት ሌላውን ተሳታፊ ወይም ፓርቲ የሚያንኳስስ፣ ክብሩን የሚነካ ወይም የጥላቻ ንግግር ከመጠቀም መቆጠብ አለባቸው። (**አንቀጽ** 11 **ንዑስ አንቀጽ** 1)
- **ውሳኔዎችን የማክበር ግዴታ፦** በውይይቱ መድረክ በጋራ ስምምነት የሚደረሱ ውሳኔዎችንና የተፈረሙ ስምምነቶችን የማክበርና የመተግበር ግዴታ። (**አንቀጽ** 11 **ንዑስ አንቀጽ** 4)

3. **የአሠራር ሥነ-ሥርዓቶች**
   - **አጀንዳ የመቅረጽ መብት፦** ማንኛውም ተሳታፊ ፓርቲ ለውይይት እንዲቀርብ የሚፈልገውን አጀንዳ የማቅረብ መብት አለው። (**አንቀጽ** 12 **ንዑስ አንቀጽ** 1)
   - **የመሪነትና የአወያይነት ሚና፦** ውይይቱ በገለልተኛ አወያዮች ወይም በፓርቲዎች የጋራ ስምምነት በሚመረጡ ሰዎች እንደሚመራ ማወቅ። (**አንቀጽ** 13)
   - **በስምምነት የመወሰን መርህ፦** በውይይት ወቅት የሚነሱ ጉዳዮች በተቻለ መጠን በጋራ ስምምነት (Consensus) እንዲወሰኑ ጥረት መደረግ አለበት። (**አንቀጽ** 15)
4. **ምስጢራዊነትና መገናኛ ብዙኃን**
   - **የምስጢር ጥበቃ፦** በዝግ ውይይት ወቅት የሚነሱና ምስጢር ተብለው የተለዩ ጉዳዮችን ውይይቱ ሳይጠናቀቅ ለውጭ አካል ወይም ለመገናኛ ብዙኃን አሳልፎ አለመስጠት። (**አንቀጽ** 16 **ንዑስ አንቀጽ** 1)
   - **የጋራ መግለጫ፦** የውይይቱን ውጤት በተመለከተ ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ የሚሰጠው በጋራ በሚሰየም ቃል አቀባይ ወይም በጋራ መግለጫ ብቻ መሆን አለበት። (**አንቀጽ** 16 **ንዑስ አንቀጽ** 2)

## 6. <u>በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶችና በምርጫ ተግባራት ላይ ሰላምና ጸጥታ የሚያስከብሩ የጸጥታ አስከባሪ አካላት የአሠራር ሥርዓት እና የሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 12/2013</u>

1. **አንቀጽ 9. የጸጥታ አስከባሪዎች የአሰራር ስርዓት**
   1) የጸጥታ አስከባሪዎች ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋማት የሚሰማሩት ቦርዱ ከሚመለከተው የጸጥታ ተቋም ጋር በሚያደርገው ውይይትና የጸጥታ ተቋሙ በሚያደርገው ምደባ መሰረት ብቻ ነው። በተቋሙ የሚደረገው ምደባም በተቻለ መጠን ሴት የጸጥታ አስከባሪዎችን ያካተተ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል።
   2) ለእያንዳንዱ የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋም እና የምርጫ ተግባር የሚመደበው የጸጥታ አስከባሪ ቁጥር እንደየ አካባቢው ተጨባጭ የጸጥታ ሁኔታ እና ቦርዱ ከሚመለከተው የጸጥታ ተቋም ጋር በሚያደርገው የምደባ ዕቅድ ላይ ተመስርቶ ይሆናል።
   3) በጸጥታ አስከባሪነት በምርጫ ጣቢያዎች ላይ የሚመደቡ የጸጥታ አስከባሪዎች የመራጮች ምዝገባ ወይም ድምጽ መስጠት ከመጀመሩ ቢያንስ ከአንድ ቀን በፊት በተመደቡበት የምርጫ ጣቢያ ተገኝተው አስፈላጊውን ፍተሻ ማድረግና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ማስተካከል አለባቸው።
   4) በዚህና ሌሎች ቦርዱ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶቹ ሥለሚያከናውኗቸው ዝርዝር ተግባራት ከሚመድባቸው ተቋም ወይም እንደ ሁኔታው ከቦርዱ ተገቢው ማብራሪያ ሊሰጣቸው ይችላል።
   5) ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ ወደ ተመደበበት ቦታ ሲመጣ የመደበውን የጸጥታ አስከባሪ ተቋም መለዮ (ዩኒፎርም) መልበስ ይኖርበታል።
   6) ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ ከተመደበበት የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋም ወደ ሌላ ምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት(ተቋም) ሊቀየር የሚችለው በመደበው ተቋም መደበኛ የአሰራር ሥርዓት መሰረት ብቻ ነው። ቅያሪው ወይም ዝውውሩ ለዚሁ ጉዳይ በቦርዱ በተዘጋጀ መመዝገቢያ ሰነድ ወይም በቃለ ጉባኤ እንዲሁም በሚመለከተው የጸጥታ ተቋም የመመዝገቢያ ሥርዓት ላይ ሊመዘገብ ይገባል።
   7) ማንኛውም የጸጥታ አሥከባሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ኃላፊ ጥሪ ካልተደረገለት በስተቀር ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋሙ) መግባት የለበትም።

8) በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት(ተቋም)ወይም በአካባቢው እና የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች የተመደቡ የጸጥታ አስከባሪዎች ኃላፊ በተመደቡበት ቦታ ስለሚከሰቱ አንዳንድ ሁኔታዎች አስፈላጊና ዋና ዋና መረጃዎች በተቋማቸው መደበኛ የአሰራር ሥርዓት መሰረት መመዝገብ ይኖርባቸዋል።
9) በተቋማቸው መደበኛ የአሰራር ሥርዓት መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መስጫ ሳጥን ወይም ቁሳቁስ ይዘው መምጣት ይኖርባቸዋል።

10) ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት(ተቋም) ተመድቦ በሚሰራባቸው ጊዜያት ሁሉ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል(ማስክ) ወይም ሌላ አፍና አፍንጫ በአግባቡ የሚሸፈን መሸፈኛ ማድረግን ጨምሮ የጤና መመሪያውን መተግበር ይኖርበታል።
11) ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት(ተቋም)ተመድቦ ሲሰራ ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ወይም ባጅ ሊይዝና አስፈላጊ ሆኖ በምርጫ አስፈጻሚዎች ሲጠየቅም ማሳየት አለበት።
12) ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ በምርጫ ጣቢያው ፍተሻ በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉ የጤና መመሪያውን ባከበረ መልኩ መሆን አለበት። ፍተሻ የሚደረገውም በተመሳሳይ ጾታ መሆን አለበት።
13) ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት ወይም በአካባቢው ድንገተኛ የጸጥታ ችግር ሲያጋጥም ለአካል ጉዳተኞች፣አቅመ ደካሞች፣ሴቶች፣ ህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለየ ትኩረት በሰጠ መልኩ ጸጥታ የማስከበር ተግባሩን ማከናወን አለበት።

2. **የጸጥታ አስከባሪዎች የሀይል አጠቃቀም(አንቀጽ 10)**

በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች (ተቋማት) እና የምርጫ ተግባራት በሚከናወንባቸው ስፍራዎች ሰላምና ደህንነት እንዲያስከብሩ የተመደቡ የጸጥታ አካላት ፀጥታ አስከባሪዎች፡-

1) ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) የስራ ማከናወኛ ቦታ ሊገቡ የሚችሉት በሚመለከተው የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋም የሥራ ባልደረባ ወይም ኃላፊ የእርዳታ ጥያቄ ወይም ጥሪ ሲደረግላቸው ብቻ ነው። ይሁን እንጂ በሰዎች ህይወት ወይም አካል ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል፣ወይም የቦርዱን ወይም የሰዎችን ሀብትና ንብረት ውድመት ሊያስከትል የሚችል በግልጽ የሚታይና የማይቀር ከፍተኛ አደጋ

ሲኖር ፍቃድ ወይም ጥያቄ ሳይቀርብላቸው ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋም የስራ ማከናወኛ ቦታ መግባት ይችላሉ።

2) ከአቅማቸው በላይ የሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ወዲያውኑ ለምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋሙ ኃላፊና ለራሳቸው የቅርብ አለቃ ማሳወቅ አለባቸው።

3) አስገዳጅ ሁኔታ መፈጠሩ የተላለፈለት የጸጥታ አስከባሪዎቹ የበላይ ኃላፊም በተቻለ ፍጥነት ለችግሩ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።

4) የጦር መሳሪያ ወይም ሀይል መጠቀም የሚቻለው የመጣውን ጥቃት ወይም አደጋ ከሀይል ወይም ከጦር መሳሪያ ውጪ በሌላ ማናቸውም መንገድ ማስቀረት ወይም ማስወገድ ያልተቻለና ብቸኛ አማራጭ እንደሆነ ብቻ ነው። የሚወሰደው እርምጃም ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል።

5) ከላይ በንዑስ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰው ሁኔታ ሲያጋጥም የሚመለከተው የጸጥታ ተቋሙ የበላይ አካል ወይም ችግሩ በተከሰተበት ቦታ ያለው የበላይ አዛዥ እንደአግባብነቱና እንደ ችግሩ ክብደት ሀይል ወይም የጦር መሳሪያ እንዲጠቀሙ ሊያዝ ይችላል። ከሚመለከትው የበላይ አዛዥ ትዕዛዝ ወይም ፍቃድ ሳይሰጥ ምንም አይነት ሀይልም ሆነ የጦር መሳሪያ መጠቀም አይቻልም።

   1) በምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋማት ውስጥ ወይም አካባቢ በማንኛውም ሁኔታ ተመጣጣኝ ያልሆነ ወይም ከመጠን ያለፈ ሀይል መጠቀም የተከለከለ ነው።

   2) ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ የሚወስደው የኃይል እርምጃ ተመጣጣኝና ምክንያታዊ ካልሆነ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት የሚያስጠይቀው መሆኑን መረዳትና ማወቅ ይኖርበታል።

   3) ከላይ በንዑስ አንቀፅ 4 የተመለከተውን ሁኔታን ወይም ችግሩን የፈጠረውን አካል ለማስቆም በጸጥታ አስከባሪዎቹ የሚወሰደው እርምጃ እንደቆመ፦

      ሀ) በሰዎች ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት ካለ በፍጥነት የህክምና ድጋፍ ጥሪ ማድረግ እንዲሁም እንደ ጉዳታቸው ደረጃ በቅደም ተከተል እርዳታ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

      ለ) በተቋማቸው መደበኛ የአሰራር ሥርዓት መሰረት ሥለ ጉዳዩ ዝርዝር መረጃና ሥለደረሰው ጉዳት አጠቃላይ መረጃ መያዝ ይኖርባቸዋል።

ሐ) የተፈጠረውን ችግር በአካባቢው ለሚገኝ ለሚመለከተው የጸጥታ አካል በተቻለ ፍጥነት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባቸው። አጠቃላይ ሁኔታውም በቃለ ጉባኤ ወይም በመዝገብ ላይ መመዝገብ ይኖርበታል።

መ) በተፈጠረው ችግር ምክንያት የደረሰው ጉዳት፣ የወደመ ወይም የጠፋ ንብረት፣ እንዲሁም ችግሩን በፈጠረው አካል ቁጥጥር ሥር ተይዞ ያለ የጸጥታ አሥከባሪ ካለ ሁለም ሊመዘገብ ይገባል።

4) ከላይ በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 መሰረት ኃይል መጠቀም የሚቻለው፦

ሀ) በምርጫማስፈጸሚያ ተቋሙ ውስጥ ወይም አካባቢ ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች በግልጽ የሚታይና የማይቀር በራስ፣ ወይም በሌላ ባልደረባ፣ የምርጫ ሰራተኛ፣ ወይም ሌላ ሰው፣ ወይም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ውስጥ የምርጫ ተግባር ለማከናወን የመጡ ተመዝጋቢዎችን፣ መራጮችን፣ የምርጫ አስፈጻሚዎቾን፣የፓርቲ ወይም የግል ዕጩዎችና ወኪሎችን፣ ታዛቢዎችን፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትን፣ ወይም ለተለያየ የምርጫ ሥራ በምርጫ ማስፈፀሚያ አደረጃጀቶች የተገኙ ሰዎችን ህይወትና አካል ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ግልፅ ሥጋት ሲኖርና የተቃጣን ጥቃት ወይም አደጋ ለመከላከል፣

ለ) የምርጫ ቁሳቁሶችንና ሰነዶችን ከመጥፋትና ከውድመት ለመከላከል፣

ሐ) ማንኛውንም የቦርዱን ወይም የመንግስትን ንብረት ከሥርቆት ወይም ከውድመት ለማዳን፣

5) ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች የተመደበ የጸጥታ አስከባሪ ሀይልን በቅጣት መልክ መጠቀም አይችልም።

3. **በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረ ሰው የአያያዝ ሁኔታ(አንቀፅ 11)**

1) ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ውስጥ ወይም አካባቢ ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ሰላምና ደህንነት እንዲጠብቅ የተመደበ የጸጥታ አስከባሪ በወንጀል የተጠረጠረን ሰው ሲይዝ

(በቁጥጥር ሥር ሲያውል) ተገቢውን ህግና የጸጥታ ተቋሙን መደበኛ የአሰራር ሥርዓት ተከትሎ መሆን አለበት።

2) በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋሙ) ውስጥ ወይም አካባቢ ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ሥለ ተከሰተው አጠቃላይ ሁኔታ፣ ሥለተወሰደው እርምጃ፣ ሥለተወሰደው እርምጃ አግባብነትና እርምጃውን ለመውሰድ ያሥገደዱ ሁኔታዎችን የያዘ ዝርዝር ሪፖርት ለሚመለከተው አካልና ለቦርዱ ወዲያውኑ በዕለቱ ወይም እጅግ ቢዘገይ በሁለት ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል።

## 7. <u>በምርጫ ሂደት በየደረጃው ስለሚኖር ቅሬታ አቀራረብ፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት እና አሰራር መመሪያ ቁጥር 10/2013</u>

1. **በመራጮች ምዝገባ ስለሚነሱ ቅሬታዎች እና አፈታታቸው(አንቀፅ 16)**
   1) ማንኛውም ሰው በመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለ እንደሆነ ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
   2) በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተቃውሞውን ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
   3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሰረት የሚቀርብ ቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜ ከመራጮች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚያልቅ ድረስ ነው። በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሰረት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከመቋቋሙ በፊት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ተቀብሎ በማስቀመጥ ኮሚቴው እንደተቋቋመ ወዲያውኑ የቀረቡትን ማመልከቻዎች ለኮሚቴው ያስረክባል።
   4) የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንዑስ አንቀፅ (1) ወይም (2) ለቀረበለት ቅሬታ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት። የምርጫ ጣቢያው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጉዳዩ በቀረበለት በአምስት ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ እንደሆነ ውሳኔው

በተሰጠው ወይም የአምስት ቀን ጊዜ ገደቡ እንዳለፈ በአምስት ቀናት ውስጥ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት ቅሬታ የቀረበለት የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ለቀረበለት ቅሬታ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት።
6) የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በአምሰት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ እንደሆነ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአምስት ቀናት ውስጥ አካባቢያዊ ስልጣን ባለው የፌደራል ወይም የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይለት ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው። ቅሬታ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የቀረበለትን ቅሬታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል።
7) የምርጫ ጣቢያው የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ሥራውን ያከናውናል። ነገር ግን የምርጫ ክልሉን ውሳኔ የሚሽር የፍርድቤት ውሳኔ የደረሰው እንደሆነ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

2. **በእጩዎች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ቅሬታዎች(አንቀፅ 17)**

   1. ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በእጩነት ከመመዝገብ የተከለከለ እንደሆነ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
   2. አንድ በእጩነት የተመዘገበ ሰው በእጩነት መቅረብ የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
   3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሰረት የሚቀርብ ቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜ ከእጩዎች ምዝገባ ቀን ጀምሮ የተመዘገቡ እጩዎች ጊዜያዊ ዝርዝር ይፋ ከሆነበት ቀን ቀጥሎ ባሉት ሁለት ቀናት ውስጥ ይሆናል።
   4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) ወይም (2) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል።
   5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ወይም የግል እጩ በምርጫ

ክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለሚቋቋም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰባት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

6. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (5) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን በመመርመር በሰባት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል። የምርጫ ክልሉም የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ስራውን ያከናውናል።
7. የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰባት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ እንደአግባቡ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም ቅሬታው የተነሳው በአዲስ አበባ ወይም ድሬደዋ ውስጥ ከሆነ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው። ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን ቅሬታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
8. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ የሚቀይር ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ የምርጫ ክልሉ ፅ/ቤት በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት ስራውን ያከናውናል።

3. **በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ቅሬታዎች(አንቀፅ 18)**

1. አንድ የተመዘገበ መራጭ ድምፅ ከመስጠት ሲከለከል ቅሬታውን ወዲያውኑ ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በማቅረብ የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከመጠናቀቁ በፊት ውሳኔ የማግኘት መብት አለው። ቅሬታው ድምጽ ከመስጠት በተከለከለው እጩ ወይም በወኪሉ ሊቀርብ ይችላል።
2. ቅሬታ የቀረበለት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴም ጉዳዩን በማጣራት፦
   ሀ) መራጩ ድምፅ የመስጠት መብት እንዳለው በመወሰን ድምጹን እንዲሰጥ ሊወስን ወይም
   ለ) ቅሬታ አቅራቢው ለዚሁ በተዘጋጀው ፖስታ ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ቅሬታ አቅራቢው ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አመልክቶ የተሰጠው ድምጽ ትክክለኛ ድምጽ ነው ተብሎ እንዲወሰንለት እንዲጠይቅ ይገልጽለታል ወይም

ሐ) ድምጽ ከመስጠት የተከለከለ ሰው በማያጠራጥር ሁኔታ ድምጽ የመስጠት መብት የሌለው ሰው ነው ብሎ ካመነ የቀረበውን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ አመልካቹ ድምጽ እንዳይሰጥ ይወስናል።

3. በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) በተመለከተው መሰረት ጊዜያዊ ድምጽ የሰጠ መራጭ ወዲያውኑ ቅሬታውን ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። ፍርድ ቤቱም የድምጽ ማዳመሩ ሂደት ውሳኔውን እስኪሰጥ ድረስ እንዲዘገይ ሊያዝ ይችላል፤ በቀረበው ቅሬታ መሰረት ፍርድ ቤቱ ቅሬታ አቅራቢው የመምረጥ መብት አለው ብሎ ከወሰነ የተሰጠው ጊዜያዊ ድምጽ ተቀባይነት ያገኛል።
4. ቅሬታ አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት የተወሰነውን ውሳኔ ለሚመለከተው ለምርጫ ክልል ጽ/ቤት ማስረከብ ይኖርበታል።
5. ከላይ በንዑስ አንቀፅ (2)(ለ) መሠረት ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠው ቅሬታ አቅራቢ በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም በፍርድ ቤት ጊዜያዊ ድምጹ እንዲፀናለት ከተወሰነለት እና እራሱ ወይም ህጋዊ ወኪሉ የድምፅ ማዳመሩ ሰዓት ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ጣቢያው ውሳኔውን ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ሳይቆጠር ውድቅ ይደረጋል።
6. አንድን መራጭ ድምፅ መስጠት የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ቅሬታ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ከላይ ድምፅ እንዳልሰጥ ተከለከልኩ የሚል ቅሬታ የሚታይበት አሰራር በተደነገገው መሠረት ቅሬታውን በየደረጃው በፅሑፍ የማቅረብና ውሣኔ የማግኘት መብት አለው። የአንድን ሰው ድምፅ የመስጠት መብት የሚቃወም የእጩ ወኪል ቅሬታውን በየደረጃው አስቀርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
7. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (6) የተመለከተው ቅሬታ የቀረበለት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጉዳዩን በማጣራት፦

   ሀ) የቀረበውን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ ቅሬታ የቀረበበት ሰው ድምጽ እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል ወይም

   ለ) ያቀረበው ቅሬታ መጣራት ያለበት ሆኖ የታየው እንደሆነ ቅሬታ የቀረበበት ሰው ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ እና ድምፁ ለብቻ በፖስታ እንዲታሸግ

በማዘዝ ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታ የቀረበበት ሰው መምረጥ የለበትም ለማለት ያስቻለውን ማስረጃ ጉዳዩን አይቶ ለሚወስነው የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይኖርበታል።

ሐ) እንደሁኔታው ከምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም አግባብነት ካለው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድቤት ቅሬታ የቀረበበት ሰው ድምፅ የመስጠት መብት የለውም የሚል ውሳኔ የድምፅ ማዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ካላመጣ የተሰጠው ጊዚያዊ ድምፅ እንዲቆጠር ይደረጋል።

መ) ድምጽ እንዳይሰጥ ቅሬታ የቀረበበት ሰው በማያጠራጥር ሁኔታ ድምጽ የመስጠት መብት የሌለው ሰው ነው ብሎ ካመነ የቀረበውን ቅሬታ በመቀበል አመልካቹ ድምጽ እንዳይሰጥ ይወስናል።

## 4. በቆጠራ ሂደትና በውጤት ላይ ስለሚነሱ ቅሬታ ዎችና አፈታታቸው(አንቀፅ 19)

1. በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤቱ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወይም ወኪል ቅሬታውን ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወዲያውኑ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል። የምርጫ ጣቢያው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ በማየት ወዲያውኑ ወይም ቢዘገይ ቅሬታውን በተቀበለ በ12 ሰዓት ውስጥ ውሳኔውን በፅሁፍ መስጠት አለበት።
2. በኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሁለት ቀናት ውስጥ ለምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል። የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ ቅሬታውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሁለት ቀናት ውስጥ በቀረበለት ቅሬታ ላይ ውሳኔ በጽሑፍ ይሰጣል።
3. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ቅሬታ የቀረበው በምርጫ ክልሉ በተደረገው የድምፅ ማዳመር እና ውጤት ሂደት ላይ ከሆነ ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን በሁለት ቀን ውስጥ ምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ አለበት። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴውም ውሳኔውን ቅሬታው በደረሰው በ12 ሰዓት ውስጥ ይሰጣል።
4. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (3) መሠረት የቀረበ ቅሬታ ላይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን እንደሁኔታው ለቦርዱ ወይም ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ከታች

በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (5) እና (9) ላይ በተደነገገው መሰረት አቅርቦ ውሳኔ ማግኘት ይችላል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የምርጫ ክልሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው በአምስት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል። ቦርዱ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

6. ከላይ በንዑስ አንቀፅ (2) እና (4) መሠረት ቅሬታ የሚያቀርብ ማንኛውም የምርጫ አስፈፃሚ፣ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩ ወይም ወኪል፤ ለምርጫ ጣቢያ ወይም ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቀረበውን ቅሬታ እና የተሰጠውን ውሳኔ ከሚያቀርበው ቅሬታ ጋር ማያያዝ አለበት።

7. የምርጫ ጣቢያው ወይም የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ፦
   ሀ) ውሳኔ እስኪሰጥ ወይም ማጣራት እስኪደረግ ድረስ ቆጠራው እንዲቋረጥ፣
   ለ) ቅሬታ የቀረበበት ቆጠራ እንደገና እንዲካሄድ፤
   ሐ) ቅሬታ የቀረበበት ቆጠራ ትክክል ስለሆነ ቅሬታው አግባብነት የለውም በማለት፤
   መ) የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በቆጠራ ላይ የቀረበው ቅሬታ የምርጫ ጣቢያውን ወይም የምርጫ ክልሉን አጠቃላይ ውጤት በመሠረቱ የማይለውጠው ከሆነ ድጋሚ ቆጠራ ማካሄድ አያስፈልግም በማለት ሊወስን ይችላል።

8. ቦርዱ በቅሬታ መልክ የቀረበለትን የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ሊያጸናው፣ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል። በተጨማሪም ቦርዱ የሕግ ጥሰት የተከሰተ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 148 መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ እንዲሁም እንደ ጉዳዩ ክብደት ጉዳዩን ለሚመለከተው የህግ አስከባሪ አካል ሊመራው ይችላል።

9. ቅሬታ አቅራቢው ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ውሳኔ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በአስር ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል።

10. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከላይ በንዑስ አንቀፅ 9 መሠረት ለቀረበለት ቅሬታ ይግባኙ በደረሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

11. በሕግ ከተሰጣቸው ሌሎች ስልጣኖች በተጨማሪ ቦርዱ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደ ቅደም ተከተላቸው በአዋጅ ቁ. 1133/2011 አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 20 እና አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 4 እና በአዋጁ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) እንዲሁም ቦርዱ የድጋሚ ምርጫ አተገባበርን በሚመለከት ባወጣው መመሪያ መሰረት ዳግም ምርጫ እንዲካሄድ ሊያዙ ይችላሉ።

12. የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ ቦርዱ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅሬታ የቀረበበትን የምርጫ ክልል ወይም ክልሎች ውጤት እንዳይገለጽ ሊያዝ ይችላል።

**“ኢትዮጵያን ወደ ተምሳሌት ሀገር!”**